# እነ "ጆን ጂሃዲ"ን የማያሰርግ የፀረሽብር ህግ

ክፍል ሁለት

አዲስ ቶልቻ

03-18-15

በዚሁ ርዕስ በቀረበ ክፍል አንድ ፅሁፍ፣ ኢትዮጵያ የአይ ኤሱን አንገት ቀዪ ጆን ጂሃዲ ጋደኛና የዓላማ ተጋሪ አሊ አዶረስ ከሁለት ዓመት በፊት በቁጥጥር ስር አውላ ማስቀጣቷን መነሻ በማድረግ የአይ ኤስን እንቅስቃሴና ኢትዮጵያ ያለባት የሽብር ተጋላጭነት ምን እንደሚመስል ተመነልከተናል። በዚህ ክፍል ሁለት ፅሁፍ ደግሞ እስላማዊ አክራሪዎች ኢትዮጵያ ላይ አይናቸውን እንዲያሳርፉ ያደረጋቸውን ሁኔታና ከአውሮፓ ሃገራት ባልተናነሰ ጥብቅ የሽብር ህግ አስፈላጊ የሚያደርገውን ሁኔታ እንመለከታለን።

እንግዲህ ኢትዮጵያ ጥብቅ የፀረሽብርተኝነት ህግ እንድታወጣ ያሰገደዳትን የሽብር ስጋት ለመረዳት አልቃይዳ/ አልሸባብ ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ ውስጥ ሊያደራጃቸው የሞከራቸውን አሸባሪ የጆሃድ ቡድኖች ተመልክትናል። በመቀጠል ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ በጂሃድ ቡድን ሊፈፀም የሚችል ተጨባጩ የሽብር ስጋት መኖሩን ለመረዳት አልቃይዳ/አልሸባብ ኢትዮጵያ ውስጥ የጂሃድ ቡድን ለማደራጀት እንዲነሳሳ ያደረገውን ነባራዊ ሁኔታ እንመለከት።

በዚሁ ርዕስ በቀረበው ክፍል አንድ ፅሁፍ  የተገለፁት እውነታዎች ኢትዮጵያ ባለፉ ሦስት ዓመታት ብቻ ሦስት የአልቃይዳ አልሸባብ አሸባሪ ቡድን የጂሃድ ግንባሮች ዒላማ መሆኗን ያመለክታሉ፤ ቡሳ ሰገል፣  ሃረከቱል ሸባብል ሙጃሃዲን ፊ ቢላድ ሂጅራይተን እና ካኦርጃ፡፡  ከዚህ ቀደም ሲልም አልኢትሃድ፣ ካዋርጂያ፣ የተሰኙ የሽብር ግንባሮች ጥቃቶች ዒላማ ሆና እንደነበር ይታወሳል። እነዚህ እንግዲህ ከሃይማኖት ሽፋን ውጭ በቀጥታ በኢትዮጵያውያን ከተደራጁት ኦነግ፣ ኦብነግና ግንቦት 7 በተጨማሪ ማለት ነው። ሁሉም ግን በተለይ ባለፉ አምስትና ስድስት ዓመታት ከሙከራ ያለፈ የሽብር ተግባር ለመፈፀም የሚችሉ ለመሆን አልበቁም።

እነዚህ ዓለም አቀፍ አሸባሪ ጃሃዲስቶች ከቅርብ ግዜ ወዲህ አይናቸው ኢትዮጵያ ላይ ያነጣጠረው ያለምክንያት አይደለም። ለጅሃድ ሽብር የሚያሰልፏቸውን ወጣቶች እንደልብ መዛቅ የሚችሉ ሆኖ ስለታያቸው ነው። ይህን እንዲያስቡ ያደረጋቸው ምክንያት አለ። ይህም በተለይ ባለፉ ሦስት ያህል ዓመታት በአዲስ አበባና በተወሰኑ የአገሪቱ ከተሞች የሚስተዋለው  ሁከት አዘል የአክራሪነት እንቅስቃሴና ይህ ያስከተለው የአክራሪነት ዝንባሌ ነው። እርግጥ ከዚህ ሁከት ቀመስ እንቅስቃሴ ጀርባም ዓለም አቀፍ አሸባሪዎቹ አሉ።

ይህ በከተማዎች አካባቢ በተለይ በአዲስ አበባ ይስተዋል የነበረውን የሙስሊሙን ሕብረተሰብ ተገቢ ጥያቄ ከለላ አድርጎ ወደሕዝቡ ዘልቆ የነበረ ሁከት ቀመስ የአክራሪነት እንቅስቃሴ፣ በአብዛኛው ከጀርባው ያለውን አደገኛ ሁኔታ ባልተረዱ ሥሜታዊ ወጣቶች የታጀበ ቢሆንም፣ ከዓለም አቀፍ የሽብር መረብ ጋር የተሳሰረበት ሁኔታ መኖሩን የሚያመለክቱ ማስረጃዎች

ግን አሉ። ከሁለት አመት በፊት በአንዋር መስጊድ የአርብ የፀሎት ስርአት በሚታወከበት ወቅት ከሳኡዲ አረቢያ የገቡ አክራሪዎች ሁከቱን ለመቀላቀል ሲሞክሩ በቁጥጥር ስር ውለው ከአገር መባረራቸው እንዲሁም የአይ ኤሱ አራጅ የጆን ጂሃዲ ወይም እንግሊዛዊው መሃመደ አሙአዚ ጓደኛና አጋር የሆነው እንግሊዛዊው አሊ አዶረስ፣ ይህ የአክራሪነት እንቅስቃሴ በተጀመረበት እ ኤ አ በ2011 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ መግባቱን ለዚህ አሰረጂነት መጠቀስ ይቻላል።

ባለፉ ጥቂት ዓመታት፣ በአንድ ወገን የጂሃድ ጦርነት የሚያካሂዱ የታጠቁ አሸባሪዎችን የማደራጀት ተግባር እየተከናወነ በሌላ በኩል የሃይማኖትና የእምነት ነፃነት የተጣሰ አሰመስለው በከተማዎች አካባቢ ቅስቀሳ በማደረግ ጀሌዎችን በማደራጀት ሁከት የሚቀሰቀስበት ሁኔታን አስተውለናል። በዚህ ሁኔታ በአክራሪነት አመለካከት የተጠመቁና በስሜታዊነት ለሁከት የተነሱ ወጣቶች፣ በትጥቅ ለሚካሄደው ጂሃድ ተዋጊነት ለመመለመል ቅርብ ናቸው። በዚሁ መሰረት በአንድ በኩል ቡሳ ሰገል፣ ሃረከቱል ሸባብል ሙጃሃዲን ፊ ቢላድ ሂጅራይተን የተባሉ የጂሃድ ቡድኖች ሲደራጁ በሌላ ወገን በከተማዎች አካባቢ “መንግስት በሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ ገባ፣ የተለየ አስተምህሮ በግድ እንዲሰበክ ተደረገ፣ ወኪሎቻችን ታሰሩ ምንትስ ቅብጥርስ” የሚል ቅስቀሳ በማካሄድ ሥሜታዊ ወጣቶች ሲመለመሉ ቆይተዋል።

ከዚህ በተጨመሪ እ ኤ አ በ1999 ዓ/ም የከሰመው የኳታር ሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ አባል የነበሩትና በሙስሊም ብራዘርሁድ ፓርቲ የአክራሪነት አስተምህሮ የተቃኘ የከተማ ሁከት የሚቀሰቀስበትንና የሚመራበትን ሥልት በማሰልጠን የሚታወቁት ዶ/ር ጃሺም ሱልጣን አሰልጥነው ያሰማሩዋቸው ኢትዮጵያውያን ከሶስት ዓመት በፊት የተቀሰቀሰውን ሁከት ቀመስ እንቅስቃሴ በመምራት መሳተፋቸውን የብሄራዊ የመረጃ ደህነትና የፌደራል ፖሊስ የጋራ የፀረሽብር ግብረሃይል መረጃ ይጠቁማል።

ይህ በከተማዎች አካባቢ የፈጠራ ወሬ በመንዛት ሙስሊሙን ውዥንብር ውስጥ በመከተት እንዲያኮርፍ የማድረግ አካሄድ፣ ሁከት ለመቀስቀስ ከማገዝ በተጨማሪ ለጅሃድ ጦርነት ያሸመቁ አሸባሪ ቡድኖች፣ ተዋጊዎችን በቀላሉ ለመመልመል የሚያመቻቸውን ሥነልቦናዊ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።

በአጠቃላይ አልቃይዳ/አልሸባብ ኢትዮጰያ ውስጥ የጂሃድ የሽብር ቡድን እንዲያደራጅ በማነሳሳት ረገድ፣ በአዲስ አበባና በአንዳንድ የሃገሪቱ ከተሞች የተቀሰቀሱት የአክራሪነት ስሜቶችና እንቅስቃሴዎች ትልቅ ድርሻ ነበራቸው ማለት ይቻላል። እነዚህ አዋኪዎች የሃይማኖትና የእምነት ነፃነት፣ እንዲሁም የሃይማኖትና የመንግስት መለያየት በሕገመንግስት የተረጋገጠ ጉዳይ ሆኖ ሳለ፣ መንግስት በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ የገባ አስመስለው በመቀሰቀስ፣ ኢትዮጳያን የአልቃይዳ/ አልሸባብ የአይን ማረፊያ እንድትሆን አድርገዋል።

ሌሎች በኢፌዴሪ ሕገመንግስታዊ ሥርአት ላይ ጭፍን ጥላቻ ያላቸውና ውጤቱ ምንም ያህል አገርን ለከፋ አደጋ የሚያጋልጥ ቢሆን፣ መንግስትን ያስወግዳል ብለው ከገመቱ ከማንኛውም ወገን ጋር ለመተባበር ዝግጁ የሆኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የአመለካከት አራማጆቻቸው የሆኑ የግል ፕሬሶችም ኢትዮጵያ የአልቃይዳ/አልሸባብ የአይን ማረፊያ እንድትሆን በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ተጫውተዋል።

እነዚህ ወገኖች በአሁኑ ግዜ በአፍጋኒስታን፣ በኢራቅ፣ በፓኪስታን፣ በሶማሊያ፣ ናይጄሪያ ወዘተ እየተካሄደ ያለው የአክራሪዎች የጂሃድ የሽብር ጦርነትና ጥቃት የኢትዮጵያም እጣ ፈንታ እንዲሆን ይፈልጋሉ፤ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ። አንድ ሁሉም ወገን በግልፅ ማወቅ የሚገባው ጂሃዲስት አሸባሪዎች ከሃይማኖትና ከእምነት ነፃነት መከበር ጋር የሚያገናኛቸው አንዳችም ነገር ያለመኖሩን ነው። እምነታቸው በአክራሪነት አመለካከት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የእምነትና የሃይማኖት እኩልነትንና ነፃነትን አይቀበሉም። በእስልምና ሃይማኖት ክልክል የሆነው፣ ንፁሃን ሰዎችን ዒላማ በማድረግ በአሰቃቂ ሁኔታ ግድያ መፈፀም፣ ማገት፣ አንገት መቅላት … ዋና መለያቸው ነው። የግድያና የጠለፋ ሰለባዎቻቸው የየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ ሊሆኑ ይችላሉ። ከእነርሱ አስተምህሮ ጋር የማይስማሙ ወይም አይስማሙም ተብለው የሚታሰቡ ሙስሊሞችም የጥቃታቸው ሰለባዎች ናቸው።

አክራሪ ጂሃዲስቶቹ ባሻቸው መንገድ የተረጎሙት፣ በአብዛኛው ዘመኑ የግድ ከሚለው የኑሮ ዘይቤ ጋር ፍፁም የማይጣጣም፣ እንዲያውም የሚጣረስ በተለይ ሃይማኖቱ ያዘዘውን ያህል እንኳን የሴቶችን መብትና ነፃነት የማያከብር አስተምህሮ ለመጫን የሚፈለጉ ጨቋኞች ናቸው፡፡ ቦኮሃራም እያደረገ ያለውን ለዚህ አስረጂነት መጥቀስ ይቻላል። .

የጂሃድ ተዋጊ ቡድኖች ሽብርን እንደትርፋማ ሥራ የሚቆጥሩ የሽፍትነት ባህሪ ያላቸው መሆናቸውም ሊታወስ ይገባል። በተለያየ መንገድ በሚሊየን ዶላር የሚለካ ገንዘብ እጃቸው ይገባል። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት አደንዛዥ ዕፅ የማዘዋወር ተግባር ውስጥ እጃቸውን የሚያስገቡበት ሁኔታም የተለመደ ነው። ይህ ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኝ “ሥራ” ነው።

ከእስላማዊ አክራሪነትና ሽብርተኝነት ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ በአጭሩ ከላይ የተገለፀውን ይመስላል። ይህ ስጋት የኢትዮጵያ ብቻ አይደለም። በርካታ የዓለም ሃገራት የጋሩታል። አሜሪካና የአውሮፓ ሃገራትም የዚህ የአክራሪነትና ሽብርተኝነት ከፍተኛ ስጋት አለባቸው። ስጋት ብቻ ሳይሆን የሽብር ጥቃት ሰለባዎችም ናቸው። የምእራባውያኑን የሽብር ስጋት ከኢትዮጵያ የሚለየው እነርሱ ያለባቸውን የሽብር ስጋት ለመከላከል የሚያወጡት የፀረሽብርተኝነት ህግ ምንም ያህል ጥብቅ ቢሆን፣ በሽብር ተጠርጣሪዎቸ ላይ ምንም አይነት ህጋዊ እርምጃ ቢወስዱ “ሰብአዊ ሙብት ጣሳችሁ” እያለ የሚነዘንዛቸወ የለም። ኢትዮጵያ ግን በእነዚህ ሃገራት ትነዘነዛለች። የአወሮፓውያኖቹን መንግስታት ፊት ያሰተዋሉ ፅንፈኛ ተቃዋሚዎችም ሃገሪቱ በተጨባጭ ያለባትን የሽብር ጥቃት ችላ በለው የፀረሽብርተኝነት ሀጉን “ይሰረዝ” እሰከማለት በደረሰ ግድየለሽነት አፋቸውን የሚከፍቱበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህን የሚያደርጉት የአውሮፓውያኖቹን ድጋፍ እናገኛለን በሚል ስሌት መሆኑ ግልፅ ነው።

የአወሮፓ ሃገራት ሽብርተኝነትን ለመከላከል የያዙትን አቋምና ህጋቸውን ምን ያህል ጥብቅ እያደረጉ እነደሆነ ለመረዳት በቅርቡ በፈረንሳይ የተፈፀመውን የሽብር ጥቃት ተከትሎ፣ በተለይ የፈረንሳይና የእንግሊዝ መንግስታት የያዙትነ አቋም እንመልከት።

በታህሳስ ወር ማገባደጃ ላይ በፈረንሳይ ፓሪስ የተፈፀመውን የሽብር ጥቃት በዙዎቻችን የሃገራችንን ጉዳይ የምናውቀውን ያህል እናወቀዋለን፤ ሰፊ የዓለም አቀፍ ሚዲያ ሽፋን ተሰጥቶት። የፈረንሳዩ የሽብረ ጥቃት ታህሳስ 29 እና 30፣ 2007 ዓ/ም በሁለት

የተለያዩ የፓሪስ ከተማ ሰፈራዎች፣ ተመሳሳይ ዓላማ ባላቸው አሸባሪዎች የተፈፀመ ነበር። የመጀመሪያው ሻሪፍ ኩዋቺ እና ሰኢድ ኩዋቺ የተባሉ 32 እና 34 ዓመት እድሜ ባላቸው ትውልደ አልጄሪያ ፈረንሳውያን ወንድማማቾች የተፈፀመ ነበር። የእነዚህ ወንድማማቾች የሽብር ጥቃት ቻርሊ ሄብዶ የተሰኘ ቧልት ቀመስ የዘት ያለው መፅሄት ጋዜጠኞች ላይ የተፈፀመ ነው። የመፅሄቷ አዘጋጆችና ጋዜጠኞች የኢዲቶሪያል ስበሰባ ላይ እያሉ የተሰነዘረውና ጋዜጠኞቹን ዒላማ አድርጎ የታቀደው ይህ የሽብር ጥቃት ለ8 ጋዜጠኞችና አራት ፖሊሶች በድምሩ ለ12 ሰዎች ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል።

የመፅሄቷን ጋዜጠኞች ዒላማ ያደረገው የሽብር ጥቃት በአካባቢው ፀጥታ በማስከበር ስራ ላይ ተሰማርተው ለነበሩ ፖሊሶችም ተርፏል። ፈረንሳይ  የቻርሊ ሄብዶ ጋዜጠኞችን ጨምሮ በ12 ዜጎቿ ላይ የተፈፀመው የሽብር ጥቃት ድንጋጤ ሳይለቃት አማዲ ኩሊባኒ የተባለ ሌላ ትውልደ ሞሮካዊ ፈረንሳዊ በአንድ የሴት የፖሊስ መኮንን ላይ ጥቃት ፈፅሞ ከፉኛ ያቆስላታል። የፖሊስ መኮንኗ ከቀናት በኋላ ህይወቷ አልፏል። የፖሊሰ መኮንኗን ለሞት ያበቃ ጥቃት የፈፀመው ኩሊባኒ ይህን እንዳደረገ  በኋላ አምልጣ ሶሪያ የአይ ኤስ አባላትን ከቀላቀላለች  ሃያት ቦሜዴን የተባለች ፈረንሳዊት ጋር በዛው በፓሪስ ወደሚገኝ አንድ የይሁዳውያን ሱፐር ማርኬት በመግባት አስራአምስት ያህል ሰዎችን ማገታቸውንና በመጨረሻም ከታጋቾቹ መሃከል አራት ያህሉን መግደላቸውን እናስታውሳለን።  በጨረሻ ሶስቱም አሸባሪዎች በፈረንሳይ ፖሊሰ ተገድለዋል። ሃያት ቦሜዴን ግን አይ ኤስን ተቀላቅላለች።

ይህን ተከተሎ የፈረንሳይ መንግስት በሌሎችም አካባቢዎች ተመሳሳይ ጥቃት እንዳይፈፀም  ከአስር ሺህ በላይ የፖሊስ ሰራዊት ነበር ያሰማራው። ውሃ የማያስገባ ጥብቅ የፀረሽብር ህግ አላት በምትባለው ፈረንሳይ፣ የፈረንሳይ ዜግነት ባላቸው ሰዎች የተፈፀመው ይህ የሽብር ጥቃት፣ ፈረንሳይ፣ እነደሚወራው የፀረ ሽብር ህጓ ውሃ የማያስገባ አለመሆኑን ያጋለጠ ነበር።  እ ኤ አ ከ1996 እስከ 2012 ዓ/ም ባሉት አንድ ተኩል አስር አመታት አሜሪካ በራስዋ ምድር ላይ 9/11 በመባል የሚታወቀውን ታሪካዊውን የሴፐተምበር 11ን የሽብር ጥቃት አሰተናግዳለች። እንግሊዝ 7/7 በመባል የሚታወቀውን የጁላይ 7 ይሽብር ጥቃት በሃገሯ ላይ አሰተናግዳለች። በዚህ ወቅት ፈረንሳይ  በአወሮፓ ሽብርተኝነትን በመከላከል ብቃቷ አውራ ሆና ለመታየት በቅታ ነበር።

የፈረንሳይ ደህንነት፣ አክራሪ የጂሃድ ተዋጊዎችን የግንኙነት መረብ የመበጣጠስ በቃቱ ድንቅ ነበር። የፖሊስ ሰራዊቷም ብረቱ፣ የፀረሽብርተኝነት ህጓም “የማያፈናፍን” የሚባልለት ነበር። ይሁን እንጂ በዚህ ሁኔታ አልዘለቀችም። የደህንነት መዋቅሯን፣ የፖሊስ ሰራዊቷንና የፀረሽብርተኝነት ህጓን ለፈተነ የሽብር ጥቃት ተጋልጣለች። ፈረንሳይ ከ2012 ዓ/ም በኋላ ባሉት ዓመታት የሽብረ በትሮችን ቀምሳለች፣ ለሶስት ገዜ ያህል። ከሁለት ወር በፊት የተፈፀመውና ለ17 ዜጎቿ ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው የሽብር ጥቃት በትር ሕመም ግን በተለየ አኳሆን ዘልቆ ተሰምቷታል።

ታዲያ ፈረንሳይ የሽብር በትር የሰነዘሩባት የጉዲፈቻ ዜግነት ከሰጠቻቸው ዜጎቿ የተወለዱ፣ አስተምራ ያሳደገቻቸው ልጆቿ “የሽብር ጥቃት ሊሰነዝሩባት እነደሚችሉ የሚያመለክቱ ተጨባጭ ማሰረጃዎቸ ነበሩ። እ ኤ አ ከ2012 በኋላ የተፈፀሙ ሶስት የሽብር ጥቃቶች ፈፃሚዎችን የፈረንሳይ ደህንነቶች የሽብር ጥቃት ከመፈፀማቸው በፊት ያውቋቸው ነበር።  ፈረንሳይ ህመሙ ዘልቆ የተሰማትን  የሽብር ጥቃት ከፈፀሙት አሸባሪዎቸ መሃከል ሁለቱ፣ ማለትም ወንድማማቾቹ ሻሪፍና ሳኢድ ኩዋቹ

በፈረንሳይ ደህንነት አይታ ስር የነበሩ ከመሆናቸው ባሻገር፣ ከዚህ ቀደም ከሽብረተኘነት ጋር ተዛማጅ በሆኑ ወንጀሎች ተከሰው የእስር ቅጣት ተወስኖባቸው ቅጣታቸውን ጨረሰው የወጡ መሆናቸው ይታወቃል። “አያፈናፍንም” ሲባልለት የነበረው የፈረንሳይ የፀረ ሽብርተኝት ህግ አነዚህን የሽብር ጥቃት ሊፈፅሙ እነደሚችሉ በደህንነቱ የሚታወቁ ሰዎችን በመከታተል ድረጊቱን እነዳይፈጽሙ መከላከል የሚያስችል ድንጋጌዎች ግን አልነበሩትም ነው የሚባለው። የከትትል ክፍተት ነበረበት። እናም ፈረንሳይ ልቧ እያወቀ የአሸባሪዎችን በትር ቀመሰች።

ታዲያ ይህ በፈረንሳይ የተፈፀመ የ17 ዜጎቿን ህየወት የቀጠፈ የሽብር ጥቃት ፈረንሳይና የተቀሩት የአወሮፓ ሃገራት የፀረሽብርተኘነት ህጋቸውን፣ በተለይ የአሸባሪዎችን የግንኙነት መረብ በመበጣጠስና እንቅስቃሴያቸውን በመገደብ እንዲሁም ተጠርጣሪዎችን በመከታተልና በቁጥጥር ስር በማዋል የመመርመር ሂደት ላይ ያለውን ክፍተት ከልሰው እንዲመለከቱ አሰገደዷል። አሁን የአውሮፓ ሃገራት የፀረሽብር ህጋቸውን እየከለሱ ይገኛሉ።

በፈረንሳይ የተፈፀመው የሽብር ጥቃት የአውሮፓ ሃገራት የፀረሽብርተኝነት ህጋቸውን እንዲከልሱ ያስገደደ ብቻ አለነበረም። ጥቃቱ በተፈፀመ ጥቂት ቀናት ውስጥ በፓሪስና በሌሎች የሃገሪቱ ከተሞች ጎዳናዎች ከሶስት ሚሊየን ህዝብ በላይ የተሳተፈባቸው የተቃውሞ ትይንቶች ተካሂደዋል። በተለይ የሽብርተኝነት ድርጊቱን በመቃወም በፓሪስ በተካሄደው ከአንድ ሚሊየን ሰዎች በላይ በተሳተፉበት ትዕይንተ ህዝብ ላይ የሃምሳ ሃገራት መሪዎች ታድመው ነበር። መሪዎቹ፣ የፈረንሳዩን ፕሬዝዳንት ፍራንሶ ሆላንዴን መሃከላቸው አድርገው እጅለእጅ ተጣምረው ለፈረንሳይ ፀረሽብር ትግል ያላቸውን አጋርነት ገልፀዋል። አጠቃላይ ሁኔታው የዓለም መንግስታት ለፀረሽብርተኝነትትግል አጋርነታቸውን ያደሱበትና ለማጠናከር ቃል የገቡበት ወይም ቃላቸውን ያደሱበት ነበር ማለት ይቻላል።

ይሁን እንጂ ባለፉ ሁለት አስርት አመታት በአለማችን የተለያዩ ሃገራት የተፈፀሙና በበዙ ሺህ የሚቆጠሩ ነውሃንን የበሉ የሽብር ጥቃቶች፣ የፓሪሱ ጥቃት ከመፈፀሙ ከቀናት በፊትና በማግስቱ የተፈፀሙ የሽብረ ጠቃቶች የዓለምን ሃገራት አጋርነት አለመቀስቀሳቸው በዙዎችን አስገረሞ አለፏል። በሌሎች ሃገራት የተፈፀሙና በሺህ የሚቆጠሩ ንፁሃን ሰዎችን ህይወት የበሉት የሽብር ጥቃቶች በየሃገራቱ ወሃ የማያስገባ የፀረሽብርተኝነት ህግ ማዘጋጀትን አሰፈላጊነት ትኩረት እነዲሰጠው አለማድረጋቸውም በዙዎች የፓሪሱን የሽብር ጥቃት ተከትሎ የተቀሰቀሰውን ስሜት በትዝብት እነዲመለከቱ አድርጓል።

የፓሪሱ ጠቃት ከደረሰ በኋላ ባሉት ጥቂት ግዜያት ውስጥ ተመሳሳይ የሽብር ጥቃት ስጋት ያለባት ኢትዮጵያ “የፀረ ሽብር ህጓን ትሰርዝ፣ አለያም ታላላ” የሚሉ ትችቶች የምእራባውያኑ ጉዳይ አስፈፃሚዎች በሆኑት ሂዩማን ራይትስ ዎችና አምነስቲ ኢንተርናሽናል የተባሉ ድርጅቶች ተሰንዝሮባታል። ይህ ኢትዮጵያውያንን እጅግ ያስገረመ ነበር።

ሂዩማን ራይትስ ዎችና አምነስቲ ኢነተርናሽናል ኢትዮጵያ የፀረሽብርተኝነት ህጓን እንድትሰርዝ ይህ ካልሆነም ድንጋጌዎቿን እንድታላላ የሚጠይቅ ሪፖርት እየቸከቸኩ ሳለ እንግሊዝና ፈረንሳይ የፀረሽብርተኝነት ህጋቸውን በምን አይነት አኳኋን ለማሻሻል እየመከሩ እንደነበረ እንመልከት።

ለዚህ ፀሁፍ ዓላማ የፀረሽብር ሕግ ማሻሻል የቀሰቀሰው የሽብር ጥቃት ሰለባ የሆነችው ፈረንሳይና ኢጋርዋ እንግሊዝ የፀረሽብር ህጋቸውን ለማሻሻል የወሰዱትን እርምጃ ላይ ነው የማተኩረው።

ፈረንሣይ ያቀረበችው የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ ማሻሻያ በዋናነት በመካከለኛው ምስራቅ የሚንቀሳቀሱ የጂሃድ ተዋጊዎችን ሊቀላቀሉ ይችላሉ ተብሎ የሚገመቱ ፈረንሳውያንን እንቅስቃሴ መገደብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የሕግ ማሻሻያው በሦሪያና ኢራቅ የሚንቀሳቀሱትን የጀሃድ ተዋጊ ቡድኖች “ሊቀላቀሉ ይችላሉ” ተብለው የሚገመቱ ፈረንሣውያንን ፓስፖርት በመቀማት ከፈረንሣይ እንዳይወጡ የሚያግድ ነው፡፡ የዚህ መነሻ የጂሃድ ተዋጊ ቡድኖችን ተቀላቅለው በአክራሪነት አመለካከት ተጠምቀው ወደ ፈረንሣይ የሚመለሱ አሸባሪዎች እንዳይፈጠሩ አሰቀድሞ መከላከል ነው፡፡ በኢራቅና በሦርያ የጀሃድ ተዋጊዮችን ተቀላቅለው የሚገኙና ቡድኖቹን ለመላቀል በሥልጠና ላይ ይሉ ፈረንሳውያን ቁጥር ቀደም ሲል ይገመት ከነበረው 550 በ2014 ዓ.ም ወደ 646 አሻቅቧል፡፡ በአጠቃላይ 3 ሺህ ያህል አውሮፓውያን የጂሃድ ቡድኖቹን ተቀላቅለው ይገኛሉ።

በፀረ-ሽብርተኝነት ሕጉ ማሻሻያ መሠረት የጀሃድ ተዋጊ ቡድኖችን ሊቀላቀሉ የሚችሉ መሆኑን የሚያመላክት በቂ ምክንያት የተገኘባቸው ፈረንሳውያን ፓስፖርታቸውን ይነጠቃሉ። በሌላ አነጋገር ከፈረንሳይ ውጭ የመነቀሳቀስ መብት ይነፈጋሉ። አሁን ባለው ሁኔታ በዚህ ማሻሻያ መሠረት በፈረንሳይ የሚኖሩ 230 ፈረንሳዊያን ፓስፖርታቸውን ይነጠቃሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የፈረንሳይ ፓርላማ የተወያየበት የፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ ማሻሻያ ሽብርተኝነትን የሚደግፉና ሽብርተኝነትን የሚያበረታቱ ድረ-ገፆችን የመዝጋት መብት ለባለሥልጣኖች ይሰጣል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችና ባለድረ-ገፆች ማንኛውንም የሽብር ጥቃት የሚያበረታታ ይዘት ያለው መልዕክት ከድረ-ገፃቸው ላይ እንዲያነሱ ማስገደድ የሚያስችል ነው፡፡ እስከ 2013 ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ የዚህ አይነት ይዘት ያላቸው መልዕክቶችን ያስተላልፋሉ በሚል 160 ድረ-ገፆች ተለይተዋል፡፡ በሕጉ መሠረት ለእነዚህ ባለድረ-ገፆች የለጠፏዋቸውን ፅሁፎች (መልዕክቶች) በ24 ሰዓታት ውስጥ እንዲያነሱ ይታዘዛሉ፡፡ ይህን ማድረግ ካልፈቀዱ ግን ድረ-ገፃቸው ይዘጋል፡፡ ሽብርተኝነትን የሚያበረታታ ፅሁፎችን የሚያወጡ የህትመት ውጤቶችም ይቀጣሉ፡፡ ቅጣቱ እስከ 7 ዓመት የሚደርስ እሥር ነው፡፡

በቅርቡ የፀረ-ሽብር ሕጓን ያሻሻለችው እንግሊዝም ከፈረንሳዩ የሽብር  ጥቃት በኋላ የፀረ-ሽብርተኝነት ሕጓን የበለጠ ጥብቅ የማድረግ ሃሳብ መኖሩን ጠቅላይ ሚኒስትሯ ይፋ አድርገዋል፡፡ በፈንሳዩ የሽብር ጥቃት ማግስት የእንግሊዙ ጠቅላይ ምኒስትር ዴቪድ ካሜሮን የአሸባሪዎችን የግንኙነት መረብ የሚበጣጥስ አዲስ ሕግ እንዲወጣ ጠይቀዋል፡፡ ዴቪድ ካሜሮን “የእንግሊዝ የደህንነት ተቋማት የተጠርጣሪ አሸበሪዎችን የግንኙነት መረብ ጥሰው በመግባት የማገድ ሥልጣን ሊኖራቸው ይገባል” ብለዋል፡፡ እንደ ካሜሮን አባባል ይህ ሁኔታ የሌሎችን ደብዳቤ ማንበብ፣  የሰዎችን የስልክ ንግግር በመጥለፍ  እስከማዳመጥ የሚዘልቅ ስልጣንን የሚያካትት ነው፡፡

እንግዲህ አምነስቲ ኢንተረናሽናልና ሂዩማን ራይትስ ዎች እነደጀርባ ላይ ቅማል ከፍ ወይ ዝቅ አልል በለው የነከሱት የኢፌዴሪ የፀረሽብርተኝነት ህግ ዓላማ፣ ልክ እንደፈረንሳይና እንግሊዝ ሃገራቱ ላይ የተጋረጠውን ንፁሃን ዜጎች ሊበላ ያሰፈሰፈውን የሽብር

አደጋ ከመድረሱ በፊት መከላከልና እደአጋጣሚ ጥቃቱ ቢሰነዘርም አሸባሪዎቹን በቁጥጥር ስር አውሎ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረገ ነው፤ በቃ። ከኢፌዴሪ ህገ ጋር ተመሳሳይ ምናልባትም የበለጠ ጥብቅ ድንጋጌዎች ያሏቸው የአውሮፓ ሃገራት "አበጃችሁ" እየተባሉ፣ ኢትዮጵያ ግን መብጠልጠሏ የኢትዮጵያውያን ህይወት "የአውሮፓውያኑን ያህል ዋጋ የለውም" ከማለት የተለየ አየደለም።

ኢትዮጵያ ቅርብና ደራሽ የሆነውን በተለያዩ ቡደኖች - አወሮፓ ውስጥ በመሸጉ ጭምር ከታወጇባት የሽብር ጥቃቶች ህዝቧን መከላለከል  የቻለችው የሽብርተኝነትን ባህሪ ያገናዘበ የፀረሽብር ህግ አውጥታ ስራ ላይ በማዋሏ መሆኑ ሊታወስ የገባል። የፀረሽብርተኝነቱን ህግ ማንሳት ወይም ማቅለል ህዝቡ የሽብር ጥቃት ሰለባ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑን ከጥቂት ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ ከነበረውና ከሌሎች ሃገራት ተሞክሮ መረዳት ይቻላል።

እንግሊዝ የሰላማዊ ሰዎችን አንገት የሚቀላው በዘመናችን ወደር ያልተገኘለትን የሽብር ድርጊት የሚፈፅመውን ጆን ጂሃዲ አሁን አያደረገ ያለውን ከማድረጉ በፊት ማስቆም አልቻለችም። ኢትዮጵያ ግን ከጆን ጂሃዲ ጋር ተመሳሳይ ዓላማ ይዞ የሰረገውን አሊ አዶረስ የተባለ እንግሊዛዊ አሸባሪ በቁጥጥር ስር አውላ ማስቀጣት ችላለች። ይህ የሆነው በፀረሽብርተኝነት ህጓ ምክንያት ነው። የአወሮፓ ሃገራት ያንዣበበባቸውን የሽብር ስጋት ከኢትዮጵያ ጋር በጋራ ለመከላከልና የመከላከል ስራው ውጤታማ እንዲሆን የኢትዮጵያ የፀረሽብርተኝነት ወሳኝ ነው። ህጉ የጆን ጂሃዲን መሰሎች ሰርገው እንዳይገቡና መጠለያ እንዳያገኙ የሚያደርግ በመሆኑ።